በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

የ4ኛ ክፍል አማርኛ(እንደ አፍ መፍቻ) የመጀመሪያ ሴሚስተር ማጠቃለያ ፈተና ማዘጋጃ ቢጋር

ህዳር/2017 ዓ.ም

መግቢያ

ይህ ሰነድ አራት ዋና ዋና የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የማጠቃለያ ፈተና ቢጋርን ያካተተ ሲሆን ር፣ የፈተና ይዘት ቢጋር፣ የክህሎት ደረጃ ቴስት ቢጋር እና የጥያቄ አይነቶች ቢጋር ናቸው፡፡ የቢጋሩ ዋና መሰረት የትምህርት ይዘቶችና ለይዘቶች የተሰጣቸው የክፍለ ጊዜ ድልድል ናቸው፡፡ የፈተና ይዘት ቢጋር ለፈተናው የተመረጡት ይዘቶችና ከእያንዳንዱ ይዘት የተውጣጣውን የጥያቄ ብዛት ይዟል፡፡ እንዲሁም የጥያቄ አይነቶች ቢጋር እያንዳንዱ ይዘት በየትኛው የፈተና አይነት እንደሚካተት ቀርቦበታል፡፡

የጥያቄዎቹ ብዛት መሰረት የሚያደርገውም ለትምህርቱ የተሰጠውን የክፍለ ጊዜ ብዛት ነው፡፡ በዚህም መሰረት ለይዘቱ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት ሲባዛ ጠቅላላ የጥያቄ ብዛት ሲካፈል ጠቅላላ የክፍለ ጊዜ ብዛት በሚል ቀመር ተሰልቶ ተዘጋጅቷል፡፡ ስለሆነም መምህራን ይህንን የቴስት ቢጋር ተከትለው ፈተናዎችን ቢያዘጋጁ ወጥ አሰራር እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ቢጋሩ የተማሪዎችን የክፍል ደረጃና የሚጠበቅ ዝቅተኛ የመማር ብቃት (minimum learning competency) መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ይህንን ተከትሎም ፈተናው በሁለት መንፈቀ ዓመት ተከፍሎ ቀርቧል፡፡ ሁለቱ መንፈቀ ዓመታት እያንዳንዳቸው 20 ጥያቄዎችን የሚያካትቱ ሲሆን በድምሩ 40 ጥያቄዎችን አካትተዋል፡፡ ከጥያቄዎች አይነት አንጻር ደግሞ 5 ጥያቄዎች እውነት/ሐሰት፣ 3 ማዛመድ እና 12 የምርጫ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ከተማሪዎች ክሕሎት አንጻር ደግሞ አብዛኛዎቹ ጥያቄዎች መካከለኛ ክብደት ያላቸው ሲሆን ቀላል እና ከባድ ጥያቄዎች ደግሞ የተመጣጠኑ ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት መካከለኛ ክብደት ያላቸው ጥያቄዎች (ግንዛቤን፣ መረዳትንና ትግበራን የሚጠይቁ) 10 (50%)፣ ዝቅተኛ ክብደት ያላቸው ጥያቄዎች (ማስታወስን የሚጠይቁ) 5 (25%)፣ እንዲሁም ከፍተኛ ክብደት ያላቸው ጥያቄዎች (ማሰላሰልን፣ ማደራጀትን፣ መተንተንንና መገምገምን የሚጠይቁ) 5 (25%) ናቸው፡፡

የማጠቃለያ ፈተና ጥያቄዎች ቢጋር

የትምህርት አይነት፡- አማርኛ

የትምህርት ዘመን፡- 2017ዓ.ም

የክፍል ደረጃ፡- 4ኛ ክፍል

የዓመቱ የክፍለ ጊዜ ብዛት፡- 180

የክፍለ ጊዜ ብዛት፡- 83

ምዕራፍ	ይዘት		የክህሎት ደረጃ			ድምር
		የክፍለ ጊዜ ብዛት	እውቀትን	መረዳትን	ትግበራን፣ ማደራጀትን፣ መተንተንንና መገምገምን የሚጠይቁ	
የመጀመሪያው መንፈቀ ዓመት						
1	የምንባብን መልእክት ማብራራት (1 እ/ሐ)	2	1			1
	የጽሑፍን ዋና ሃሳብ መለየት (1 ም)	4		1		1
	ለቃላት ዓውዳዊ ፍቺ እና ፍካሬያዊ ፍቺ ይሰጣሉ (1 አ)	6	1			1
	አያያዥ ቃል በመጠቀም ድርብ ዓ/ነገሮችን ይጽፋሉ (1 ም)	6			1	1
2	አንቀጽን አቀላጥፎ ማንበብ (1 እ/ሐ)	4	1			1
	ቃላትን ከተጨባጭ ህይወታቸው ጋር ማዛመድ (1 አ)	4		1		1
	አያያዥ ቃልን በዓ/ነገር ውስጥ መጠቀም (2 ም)	6		2		2
	የምንባብን መልእክት መግለጽ (1 ም)	3		1		1
3	የጽሑፍን ዋና ሃሳብ መለየት (1 ም)	4		1		1
	ቅጥያዎችን በመጠቀም ዓ/ነገር መመስረት (1 ም)	5			1	1
	አያያዥ ቃላት በመጠቀም ድርብና ውስብስብ ዓ/ነገሮችን መመስረት (1 ም)	6			1	1
4	ከጽሁፍ ውስጥ ዝርዝር መረጃውን መጻፍ (1 ም)	4			1	1
	የውሰት ቃላትን ጥቅም መዘርዘር (1	4			1	1

	እ/ሐ)					
	ስለ አንቀጽ ምንነት ማብራራት (1 ም)	4		1		1
	በግስ ዓ/ነገር መመስረት (1 ም)	4			1	1
5	የምንባብን ሀሳብ መግለጽ (1 እ/ሐ)	4		1		1
	የአንቀጽ ባህሪያትን መለየት (1 እ/ሐ)	4		1		1
	በአዳዲስ ቃላት ዓ/ነገር መመስረት (1 አ)	4			1	1
	ገሊጮችን በመጠቀም ዓ/ነገር መመስረት (1 ም)	4			1	1
	ድምር		3	10	7	20

ማሳሰቢያ፡- ቀጥሎ የቀረቡት ቁልፍ ቃላት በሰነዱ ውስጥ የቀረቡት በአሳድሩ ሲሆን ምህጻረ ቃላቱ የያዙት ፍቺ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

- ✓ እ/ሐ፡- ‹እውነት› ወይም ‹ሐሰት› በማለት የሚመለሱ ጥያቄዎች = 5
- ✓ አ፡- በማዛመድ የሚመለሱ ጥያቄዎች= 3
- ✓ ም፡- ከተሰጡ አማራጮች መልሶችን በመምረጥ የሚመለሱ ጥያቄዎች =12